# የሁኔታዎች ሪፖርት ማድረጊያ ስርዓት፦ ተዘውትረው የሚጠየቁ ጥያቄዎች

**ጥ.** የሁኔታ ሪፖርት ማድረጊያ ስርዓት፡ ማለትም **SpeakfullyNow**፡ በኩል ምን አይነት ክስተቶች ሪፖርት ሊደረጉ ይችላሉ?

**መ.** ማንኛዉም ተገቢ ያልሆነ ስነምግባር እንደ አድልዎ፣ ትንኮሳ፣ በቀል፣ ጉልበተኝነት፣ ሌሎች የዜጎች መብት ጥሰት ወይም ሌሎች አሳሳቢ ጉዳዮችን በ *SpeakfullyNow* በኩል ሪፖርት ማድረግ ይቻላል። ዝርዝር መግለጫዎች እና መመሪያዎች ለማግኘት፡ *https://bit.ly/cpsspeakfullynow*ን ይጎብኙ፡ ወይም በቀኝ በኩል ያለውን የ *QR* ኮድ ስካን ያድርጉ

**ጥ.** በ **Speakfully** በኩል የሁኔታዎችን ሪፖርት ማድረግ የሚችል ማን ነው?

**መ.** ማንኛውም ተማሪ፣ ተንከባካቢ፣ ወይም የሰራተኛ አባል ሪፖርት ማቅረብ ይችላል።

**ጥ.** እንዴት ነው ሪፖርት ማድረግ የሚቻለው?

**መ.** ሪፖርት ማድረግ የሚቻለው እንደሚከተለው ነው፦

- በአካል ወይም በኢሜል ለአስተማሪ፣ ለርእሰ መምህር፣ ለመመሪያ አማካሪ፣ ወይም ለሌላ የ *CPS* ሰራተኛ አባል
- በኦንላይን በ *cps.speakfullynow.com* ላይ ወይም በቀኝ በኩል ያለውን የ *QR* ኮድን በመቃኘት።

**ጥ.** ማን ሪፖርቱን ማግኘት ይችላል?

**ሀ.** የበላይ ተቆጣጣሪው ጽሕፈት ቤት፡ እንዲሁም የፍትሃዊነት፣ ማካተት እና ንብረት *(OEIB)* ቢሮ እያንዳንዱን ሪፖርት ይደርሳቸዋል። እነዚህ ሁለት ቢሮዎች፡ እንደ ክስተቱ ሁኔታ የትኛው መርማሪ መመደብ እንዳለበት ይወስናሉ። የተመደበው ግለሰብ ደግሞ የሪፖርቱን ይዘት ማግኘት ይችላል።

**ጥ.** ይህ በሚስጢር የሚደረግ ሂደት ነው? ምርመራ ለመጠናቀቅ ምን ያህል ጊዜ ይወስዳል?

**መ.** ተማሪዎችን የሚመለከት ሪፖርት ሲደረግ፡ የሚመለከታቸውን አካላት የሚንከባከቡ ተንከባካቢዎች ወዲያውኑ እንዲያውቁት ይደረጋል፡ ይህም ሪፖርቱ ከተሰጥ በኋላ በ *24* ሰዓት ውስጥ ይደረጋል። ምንም እንኳን በሚስጥር መያዙ ዋስትና ባይኖሮውም፡ የጉዳዩ ሪፖርቶች በተቻለ መጠን በሚስጥር እንዲያዝ ይደረጋል። መረጃው የሚጋራው ከ የበላይ ተቆጣጣሪው ቢሮ፣ ከ *OEIB*፣ ከተመደበው መርማሪ እና ካስፈለገ ደግሞ ከሌሎች ተገቢ የሆኑ አካል ብቻ ነው። ማንኛውም የተለየ የዲሲፕሊን መዘዞች ለሰራተኞች እና/ወይም ተማሪዎች በህግ መሰረት በሚስጢር የሚያዙ ናቸው።

ለምርመራው የሚያስፈልገው ጊዜ እንደ የሁኔታው ክስተት አይነት ይወሰናል። ለዝርዝር የጊዜ መስመር፡ እባክዎ የክስተት ሪፖርት ማድረጊያ መመሪያን በ*https://bit.ly/cpsspeakfullynow* ላይ ይገምግሙ።

**ጥ.** ስም ሳይገለጽ ሪፖርት ማድረግ እችላለሁ?

**መ.** የሚመረጥ መንገድ ባይሆንም ሪፖርቶች ማንነታቸው ሳይታወቅ ሊደረጉ ይችላሉ። አንድ ግለሰብ ማንነቱ ያልታወቀ ሪፖርት ካደረገ፡ እባክዎን አስቡበት፡ ምክንያቱም ይህ የተከሰሰውን ክስተት ለመመርመር ወይም ለመፍታት አስቸጋሪ እና አንዳንዴም የማይቻል ያደርገዋል።

**ጥ.** ከተወሰነ ጊዜ በኋላ መልስ ካልሰማሁ እና ስለሁኔታው ምን እንደተደረገ ለማወቅ ብፈልግ ምን ይሆናል?

**መ.** SpeakfullyNow ደህንነቱ የተጠበቀ የመልእክት መላላኪያ ባህሪ ስላለው፡ ለሪፖርቱ ከተመደበው መርማሪ ጋር መገናኘት ይቻላል። በሪፖርትዎ ላይ ተጨማሪ ዝርዝሮችን ማከል፣ ለቀጣይ ጥያቄዎች መቀበል እና ምላሽ መስጠት፣ እንዲሁም የሪፖርትዎን ሁኔታ ምን ላይ እንደደረሰ ማወቅ ይችላሉ፤ ከፈለጉ ይህ ሁሉ ማንነትዎን ሳያሳውቁ ማድረግ ይችላሉ።